# <u>በዋሽንግተንና አካባቢዋ የህዳሴው ምክር ቤት የአባላት እውቅናና ምስጋና ምሽት በዋሽንግተን ዲሲ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ተከበረ!</u>

በፀሃዮ ደባልቀው (ሰኔ 14 ቀን 2005 ዓ.ም.) ዋሽንግተን ዲሲ

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብ ለናይል ተፋሰስ አገሮች የትብብርና የአብሮነት መንፈስ መገለጫና ምንጭ እንጂ የፍጥጫና የጸብ መነሻ ምክንያት ሊሆን እንደማይገባው የኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ ጽኑ እምነት ነው ሲሉ አምባሳደር ግርማ ብሩ አረጋገጡ!

ተቀማጭነታቸው በዋሽንግተን ዲሲ ሆኖ በአሜሪካ፣ በካናዳና በሜክሲኮ የኢትዮጵያ ልዩ መልክተኛና ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ግርማ ብሩ ይህንን የገለጹት በዛሬው ዕለት በኤትዮጵያ ኤምባሲ አዳራሽ የዋሽንግተን ዲሲ ከተማ፣ የቬርጅኒያና የሜሪላንድ ግዛቶች የታላቁ የህዳሴው ግድብ ምክር ቤት ባዘጋጀው የእውቅንና የምስጋና ስነ ስርዓት ላይ ተገኝተው ባሰሙት ቃል ነው።



አምባሳደር ግርማ ብሩ በዚሁ ስነ ስርዓት ላይ ለተገኙት በመቶዎች የተቆጠሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የዋሽንግተን ዲሲና አካባቢዋ የህዳሴው ምክር ቤት ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ ባደረጉት የላቀ አስተዋጽኦ ባዘጋጀው የምስጋናና የእውቅና መድረክ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር ላይ ነው።

አምባሳደር ግርማ ብሩ ገና የህዳሴው ግድብ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የኢትዮጵያ መንግስት ካለው በጎ የመተባበርና ተጋግዞ የማደግ እምነቱ በመነሳት የናይል ተፋሰስ አገራት ተፈጥሮ የለገሰቻቸውን የአባይ ወንዝ ትሩፋት በፍታዊህነትና ሁሉንም በየደረጃ እንደአስፈላጊነቱ ተጠቃሚ የሚያደርገውን የስምምነት ማአቀፍ ሁሉም የተፋሰሱ አገሮች እንዲፈርሙ ሃሳቡን በማመንጨት ግንባር ቀደም ሚና መጫወቱን አውስተዋል።

አዲሱ የስምምነት ማዕቀፍ (Cooperative Framework Agreement) የምንገኝበት ዘመን በሚፈቅደው ሰላማዊ የትብብርና ሰጥቶ የመቀበል መርህ የተመረኮዘ ተነሳሽነት መሆኑን አበክረው ገልጸዋል።

አምባሳደር ግርማ ብሩ በዚሁ ንግግራቸው ወቅት ቅኝ ገዥዎች የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲሉ የተውልንን የትላንቱን ውርስ እርግፍ አድርገን በመተው የህዝቦቻችንን የጋራ ተጠቃሚነትና የአገሮቻችንን የጋራ ልማት ወደ ሚያረጋግጠው ወደ አዲሱ የአብሮነት የመተሳሰብና ተደጋግፎ የማደግ መንፈስ ልንሸጋገር ይገባል ሲሉ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።



አምባሳደር ግርማ ብሩ በዚሁ ስነ ስራዓት ላይ የተገኙት ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ላደረጉት አርአያነት ያለው ተሳትፎ የአገራችን ህዝብ በምልዓት በራሱ አቅም የህዳሴውን ግድብ እውን ለማድረግ የሚያደርገው ጥረት አካል በመሆኑ እናተም በዚሁ የተነሳሽነት ስሜት አገራችሁንና ወገኖቻችሁን ለመታደግ እና ራሳችሁንም ለመጥቀም የትውልድ አሻራችሁን በማኖራችሁ ልትኮሩ ይገባል እያልኩኝ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ በማለት ተሰታፊዎችን አበረታተዋል።

በዚሁ ስነ ስርዓት ወቅት አቶ ንጉሴ ቢራቱ የዋሽንግተን ሜትሮ አካባቢ የህዳሴው ምክር ቤት ሰብሳቢ ም/ቤቱ በአካባቢው የሚገኙት ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በግንባታው ሂደት ያደረጉትን የእስካሁኑን ግንባር ቀደም ተሳትፎ በማድነቅ እስከ ግድቡ ግንባታ ፍጻሜ ድረስና እስከ ወዲያኛውም በአገር ልማት በኩል የሚያደርጉትን ንቁ ተሳትፎ አጠናክረው እንዲቀጥሉበት ጥሪ አስተላልፈዋል።

------//-----